የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

በምዕራብ ሐረርጌ ዞን

በዶባ እና በገመቺስ ወረዳዎች በተፋሰስ ልማት የተጎዳ መሬት እንዲያገግም የተሰራ ተሞክሮ



ህዳር /2018 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ 1

ክፍል አንድ 2

1. ዓላማ 2

1.1. አጠቃላይ ዓላማ 2

1.2. ዝርዝር ዓላማ 2

2. አስፈላጊነት 2

3. ወሰን፡- 2

4. የመረጃ አሰባሰቡ ስልት፡- 2

5. የሚጠበቁ ውጤቶች፡- 3

ክፍል ሁለት 3

6. ምዕራብ ሐረርጌ ዞን 3

7. በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ለዕይታ የተመረጡ ወረዳዎች 4

7.1. ዶባ ወረዳ 4

7.1.1. በተፋሰስ ስራ ላይ በወረዳው የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 5

7.2. የወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ 5

7.2.1. የተፋሰስ ስራው ከመጀመሩ በፊት የወልቂጡማ ኢብሳ ሳይት የነበረበት ሁኔታ 6

7.2.2. ቦታው ለተፋሰስ ስራ የተመረጠበት ምክንያት 6

7.2.3. በቦታው ላይ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች 6

7.2.4. የተፈጠረ ግንዛቤ 7

7.2.5. የተከናወነ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ተግባር ስራ 7

7.2.6. 3.6.ስራውን ለማጠናከር እና ለልማቱ ቀጣይነት የተደራጀ ማህበር 8

7.2.7. የተገኘ ውጤት 10

7.2.8. ለውጤቱ ቀጣይነት የተዘረጋ ስርዓት 12

7.3. ገመቺስ ወረዳ 13

7.3.1. በተፋሰስ ስራ ላይ በወረዳው የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 13
7.4. ድንገቴ ባድያ ቀበሌ 14
7.4.1. የተፋሰስ ስራው ከመጀመሩ በፊት የድንገቴ ባድያ ሳይት የነበረበት ሁኔታ 14
7.4.2. ቦታው ለተፋሰስ ስራው የተመረጠበት ምክንያት 14
7.4.3. በቦታው ላይ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች 15
7.4.4. ስራውን ለማጠናከር እና ለልማቱ ቀጣይነት የተደራጀ ማህበር 18
7.4.5. የተገኘ ውጤት 18
7.4.6. ቦታው አሁን ያለበት ሁኔታ 19
7.4.7. ለውጤቱ ቀጣይነት የተዘረጋ ስርዓት 20
7.5. በዶባ እና በገመቺስ ወረዳዎች ከታዩት የተፋሰስ ስራ ውጤቶች ውስጥ ሊወሰድ የሚገባ ተሞክሮ .. 20
ክፍል ሦስት 22
8. ማጠቃለያ 22

መግቢያ

ዘላቂና ጤናማ ተፈጥሮአዊ በሆነ አካባቢ ውስጥ መኖር የዜጎች መሰረታዊ መብት ነው። ይህንኑ ለማረጋገጥ ደግሞ የአካባቢ መጎሳቆልን እና መራቆትን በመቀነስ የተሻለ አካባቢን ማቆየት አስፈላጊ ነው ። የተፈጥሮ ሃብቶች ታምቀው የሚገኙበት አካባቢዎች በተገቢው መንገድ ከተያዙ ዘላቂ የሕይወት ዋስትና ሆኖ መቀጠሉ አያጠራጥርም። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ አካባቢዎች ከሰው ልጅ አያያዝ፣ የጥንቃቄ ጉድለትና ከበረሃማነት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ አደጋ ተጋርጦባቸዋል። ወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ ስጋት የሆነውን አደጋ ሊከላከል የሚችል ስራ በወቅቱ ካልተሰራ ጉዳቱ የሁሉም መሆኑ ግልፅ ነው። በመሆኑም ሁሉም ተቋማትና መላው ሕብረተሰብ በሚያከናውናቸው የእለት ተእለት ተግባራት ውስጥ የአካባቢን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ ሀገሩንና ራሱን ከአደጋ ማዳን ይጠበቅበታል።

አካባቢ በአግባቡ በተያዘ ቁጥር ምቹ የአካባቢ ሁኔታና የተሻለ የአየር ንብረት ኖሮ ሕብረተሰቡ በጤንነት የመኖር እድሉ ከፍ ይላል። በመሆኑም አንድ ቦታ የተከናወነውን አስተማሪ የሆነን ስራ መረጃውን በማደራጀት እንዲሁም አሰራሩን በመተንተን ሌሎችም ቦታዎች ዘዴውንና መንገዱን ተጠቅመው እንዲሰሩ ማድረግ ጠቃሚ ነው።

በዚህም መሠረት በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሀረርጌ ዞን በዶባ እና በገመቺስ ወረዳዎች በፊት ተጎድተው የነበሩ አሁን ግን ተከልለውና ከሰውና ከቤት እንስሳት ንክኪ ነፃ ሆነው እንዲያገግሙ የተደረጉ ቦታዎች የመስክ እይታ በማድረግ እንዲሁም እንዲያገግሙ የተከናወኑ ስራዎችን በመረጃ በማሰባሰብ ሌሎች ግንዛቤ እንዲያገኙበት እና እንዲማሩበት ይህ የተሞክሮ ሰነድ ተዘጋጅቷል።

ክፍል አንድ

1. ዓላማ

1.1.አጠቃላይ ዓላማ

በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በዶባ እና ገመቺስ ወረዳዎች የተከናወኑ የአካባቢ ጥበቃ፣ የተፋሰስ ስራ፣ የአፈርና ውሃ ጥበቃ እንዲሁም የተጎዳ መሬት እንዲያገግም የማድረግ ስራን በአካል በመመልከት፣ በመረጃነት የተቀመጡ ሰነዶችን በመፈተሽ እንዲሁም ተጠቃሚዎችን በማነጋገር መረጃ ሰብስቦ በመልካም ተሞክሮነት ቀምሮ በተለያዩ ስልቶች ለሌሎች አካባቢዎች እንዲስፋፋና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ነው።

1.2.ዝርዝር ዓላማ

- **በዶባ እና ገመቺስ ወረዳዎች የተከናወነው የአካባቢ ጥበቃ ስራ በመልካም ተሞክሮነት ማደራጀት**
- **በዶባ እና ገመቺስ ወረዳዎች የተመዘገቡ ውጤቶች በተሞክሮ ተቀምረው ለልምድ እንዲስፋፋ እና ለሌሎች አካባቢዎች እንዲተገበሩ ማድረግ**

2. አስፈላጊነት

በህብረተሰቡ የተሰሩ ተሞክሮዎችን መረጃ በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመልካም ተሞክሮነት ቀምሮ ሌሎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ ከመስሪያ ቤታችን ዕቅድ ውስጥ አንዱ ነው። በመሆኑም በአንድ ቦታ የተከናወኑ መልካም ተሞክሮዎችን ቀምሮ ሌሎች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ተገቢ ነው። ይህም ዜጎች በተጠበቀ አካባቢ ለመኖር የሚያስችሉ ተግባራትን ለመፈጸም ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ነው። ስለሆነም የታዩትን ስራዎች ለማበረታታትና ለማነቃቃት እንዲሁም ልምዱን ሌሎች እንዲማሩበት ለማድረግ ይህን የግንዛቤ ማስፋፊያ የሆነውን የመልካም ተሞክሮ ቅመራ ሰነድን ማዘጋጀትና እንዲስፋፋ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

3. ወሰን፡-

ይህ ሰነድ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሀረርጌ ዞን በአካባቢ ጥበቃ ስራዎች የተከናወኑትን የተፋሰስ ስራዎች ጠቅለል አድርጎ የሚያሳይ ሲሆን ዶባ ወረዳ በወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ እና ገመቺስ ወረዳ በድንገቴ ባድያ ቀበሌ የተሰሩትንና የታዩትን የአካባቢ ጥበቃ ስራን የሚገልፅ ነው።

4. የመረጃ አሰባሰቡ ስልት፡-

መረጃውን ለማሰባሰብ የሚረዳ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት አስቀድሞ ለክልል፣ለዞን እና ለወረዳው በመላክ ይዘቱን ቀድመው እንዲያውቁት ተደርጓል። በመቀጠልም የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንደተሠማራ በቅድሚያ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ ከዞን አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ስለ አላማው ዝርዝር ሁኔታ በመወያየት በተለያየ ስልት መረጃ ተሰባስቧል። መረጃ አሰባሰቡም የተዘጋጀውን ቼክ ሊስት በመጠቀም ሲሆን

ለዚሁ ተግባር የሚጠቅሙ ሰነዶችን በመፈተሽ፣ በስራ ላይ ለመስራት የተደራጁ የማህበር አባላትን፣ ሌሎች ተጠቃሚዎችንና ባለሙያዎችን በማነጋገር እና ሥራው በተከናወነበት ቦታ ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል።

በማጠቃለያም ከዞን እና ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመረጃ አሰባሰቡ እና በመስክ ምልከታው በታዩና በተነሱ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት ተደርጎ ተጨማሪ ግብዓት ተሰብስቧል።




ፎቶ1፡- የመረጃ አሰባሰብ ስልት

5. የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የተቀመረው የመልካም ተሞክሮ ሰነድ ለሌሎች በአስተማሪነት ቀርቦ ይጠቀሙበታል
- ምልከታ የተደረገባቸው አካባቢ ያሉ ሥራተኞች፣ የማሕበር አባላት፣ ሕብረተሰብ ለተግባሩ ያላቸው ተነሳሽነት ይጨምራል
- ህብረተሰቡ ተደራጅቶ አከባቢን ማልማት እና መንከባከብ ትኩረት አግኝቶ በተለያዩ ቦታዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ

ክፍል ሁለት

6. ምዕራብ ሐረርጌ ዞን

ምዕራብ ሐረርጌ ዞን የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ሲሆን ዋና ከተማው ጭሮ ነው። ዞኑ በደቡብ አቅጣጫ ከሸበሌ ወንዝ ሲዋሰን በደቡብ ምራብ ከአርሲ ዞን፣በሰሜን ምዕራብ ከአፋር ክልል፣በሰሜን ከሶማሌ ክልል እንዲሁም በምሥራቅ በኩል ከምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ይዋሰናል።

ዞኑ 15 ወረዳዎች እና 5 የከተማ አስተዳደሮች አሉት፣ ፡የዞኑ ዋና ከተማ ጭሮ ከአዲስ አበባ ወደ ሐረር በሚወስደው የአስፓልት መንገድ ከአዲስ አበባ በ300 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኝ ነው። በዞኑ በርካታ የተፋሰስ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን የተሰራው የተፋሰስ ስራ በቅንጅት

እንደሆነ እና ከዚህ በፊት የነበረውን ችግር ለማህበረሰቡ በማስረዳት ችግሩንም በጋራ መፍታት እንደሚገባ ለማህበረሰቡ ቀድሞ ግንዛቤ ስለተፈጠረ በስራው ላይ ለመረባረብ ምቹ ሁኔታ ገጥሯል።

ዞኑ 15 ወረዳዎች እና 5 ከተሞች ይገኛሉ። በ15ቱም ወረዳዎች የተቀናጀ የተፋሰስ ስራ ተሰርቷል አሁንም እየተሰራ ነው።

በዞኑ የተሰሩ የተቀናጀ የተፋሰስ ስራ ውጤታማ የሆኑት ሁሉም የድርሻውን ስለተወጣ ነው። ቦታ ሲመረጥ ባለሙያዎችን በመጠቀም የጋራ መግባባት በመፍጠር ነው። አካባቢ ጥበቃ፣ ግብርና እና አስተዳደር አብሮ በመቀናጀት በስራው ላይ ከፍተኛ ሚናውን ተጫውቷል። ቅንጅታዊ አሰራሩ በሌሎች ወረዳዎችም የተጠናከረ ነው። ስራው ሲሰራ ባለሙያዎችን በመመደብ ሙያዊ ድጋፍ እንዲሰጡ ተደርጓል። አመራሮችም ክትትልና ድጋፉን በትኩረት ሰርተዋል። በዚህ በተቀናጀ የተፋሰስ ስራ ውጤታማነት ምክንያት በዞኑ ስር ካሉት ወረዳዎች ውስጥ የተሰሩ የተፈጥሮ ሀብት ስራዎችን በ2016 ዓ.ም እና በ2017 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ደረጃ በመታየት ገመቺስ ወረዳ በተሻለ ውጤታማነት ተመርጦ በክልል ፕረዘዳንት ጽ/ቤት የመኪና ተሸላሚ መሆን ችለዋል።

በሂደቱ የግለሰብ ማሳ ነክቶ የግለሰቦች ተቃውሞ መነሳቱ እና ችግኝ ሲተከል ደን በዝቶ ሰብል የሚያጠፋ የዱር እንስሳቶች ይፈጠሩና ሰብላችን ያልቃል በማለት ቅሬታ ያላቸው ሰዎች መፈጠራቸው ከስራው በፊት ያጋጠሙ ችግሮች ሲሆኑ ቦታው የራሳቸው ሆኖ ለምቶ በተሻለ ዘዴ መጠቀሙ እንደሚሻል ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር እና በቦታው ላይ የተፋሰስ ስራ ከተሰራ በኋላ የሚከተለውን የገቢ ምንጭ እንደ ሳር ሽያጭ፣ ንብ ማነብ እና ሌሎችን የሚያስገኙ ጥቅሞች ለማህበረሰቡ አስገንዝቦ በመተማመን ችግሩ ተፈትቷል።

7. በምዕራብ ሐረርጌ ዞን ለዕይታ የተመረጡ ወረዳዎች

ካሉት 15 ወረዳዎች ውስጥ በመስክ ስራው እንዲታዩ የተመረጡት ወረዳዎች ሁለት ሲሆኑ እነሱም ዶባ ወረዳ እና ገመቺስ ወረዳ ናቸው።

7.1.ዶባ ወረዳ

ዶባ ወረዳ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሲሆን ወጣገባ እና ተራራማ የመሬት አቀማመጥ ያለው እና ወይነ ደጋ የአየር ንብረት ያለበት ወረዳ ነው። ወረዳውን በሰሜን ሱማሌ ክልል፣ በደቡብ ጡሎ ወረዳ፣ በምስራቅ ጎሮ ጉቱ ወረዳ እና በምዕራብ ጭሮ ወረዳ ያዋስኑታል።

በወረዳው 40 የገጠር ቀበሌዎች እና 2 አነስተኛ የከተማ አስተዳደሮች ያለው ሲሆን የወረዳው ሕዝብ ብዛት ወ 112,012 ሴ 109,794 ድ 221,806 ነው። ሕብረተሰቡ በግብርና ስራ እና ከብት በማደለብ ስራ ላይ ተሰማርተው ኑሮአቸውን እየመሩ የሚገኙ ናቸው።

7.1.1. በተፋሰስ ስራ ላይ በወረዳው የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ተራራዎችን ማልማትና ከጉዳት ማዳን እንደሚገባ በመረዳት በየደረጃው ዕቅዶችንና ግንዛቤዎችን ሲያወርድ ትኩረት ከሰጠባቸው ቦታዎች ውስጥ አንዱ በዶባ ወረዳ ነው። ዶባ ወረዳም ከአካባቢ መራቆት ጉዳቶች ለመዳን ለተፋሰስ ስራው ትኩረት ሰጥቶ ከወረዳ እስከ መንደር የስራ ቡድን በመመስረት መከናወን ያለበትን በየደረጃው አቅዶ ለአመራሩ፣ ለባለሙያዎች፣ ለሀገር ሽማግሌዎች፣ ለማህበር አባላት እና ለማሕበረሰቡ በዕቅዱ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ስራ መግባት ችሏል።

ማሕበራትን በማደራጀትና የማህበሩን አባላት በመለየት ወደ ስራ የማስገባት የመምራት፣ የመደገፍ እና የማስተባበር ስራ በመስራት በስራው ላይ ሁሉም ትኩረት እንዲሰጠው ተደርጓል። የተፋሰሱን ስራ ለማከናወን የጊዜ ሰሌዳ በማቀድ ክንውኑን በመከታተልና በመገምገም ስራዎች በትኩረት እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጣል። በዚህ መሰረት የሚታዩ ችግሮችን በማጤን እና ለችግሮቹ መፍትሔ በመስጠት በዕቅድ የተመሩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከዕቅድ በመቀጠል የተከናወነው ተግባር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ሲሆን በተሰጠው ግንዛቤም ውጤት አስመዝግቧል። የሕብረተሰቡ አስተሳሰብ ተሻሽሎ በተነሳሽነት የድርሻቸውን ተግባራት በማከናወናቸው ከቀደመው ጊዜ ተሻሽሎ በአረንጓዴ የተሸፈኑ ተራራዎች በዶባ ወረዳ ማየት የተቻለ ሲሆን በወረዳው ካሉት ቀበሌዎች ውስጥ የወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌን መመልከት ተችሏል።



ፎቶ2፡- የወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ ጽ/ቤት

7.2.የወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ

ወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ የሚገኘው በዶባ ወረዳ ሲሆን የቀበሌው ጽ/ቤት ከወረዳው ዶባ ከተማ 24 ኪ.ሜ እና ከዞኑ ጭሮ ከተማ 35 ኪ.ሜ ርቀት ያለው ነው። ቀበሌው ወጣ ገባ እና ተራራማ የመሬት አቀማመጥ ያለው እና ወይነ ደጋ የአየር ንብረት ያለበት ቀበሌ ነው። በቀበሌው ወ 1,992 ሴ 1,952 ድ 3,944 ህዝብ የሚኖር ሲሆን አብዛኛው በግብርና ስራ እና ጥቂቶቹ ከብት በማደለብ ስራ ላይ ተሰማርተው ኑሮአቸውን እየመሩ የሚገኙ ናቸው።

በወልቂጤማ ኢብሳ ቀበሌ የሚኖሩ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን ከመራቆት ለማዳን በርካታ የተፋሰስ ስራ (አፈርና ውሃ ጥበቃ) የሰሩት ሲሆን ከተሰሩት ውስጥ የወልቂጤማ ኢብሳ ሳይት (ጂልባ ጨጨብሳ) የሚባለውን ሳይት ማየት ተችሏል።

7.2.1. የተፋሰስ ስራው ከመጀመሩ በፊት የወልቂጤማ ኢብሳ ሳይት የነበረበት ሁኔታ

ወልቂጤማ ኢብሳ ሳይት በተፋሰስ ስራው ከመልማቱ በፊት ፈጽሞ ዛፍ የተመናመነና ገላጣ የሆነ ቦታ ሆኖ ሰዎች ለእርሻ መሬት እየተጠቀሙበት ነበር። በቦታው ላይ በእርሻ መሬትነት ማሽላ እና ቦለቄ እየዘሩ እየተጠቀሙበት ቢቆዩም እያገኙ የነበረው ምርት በጣም ዝቅተኛ ነበር። በወቅቱ የነበረው ችግር ብዙ ምርት አለመስጠት ብቻ ሳይሆን በመሬቱ ላይ እየበቀለ የነበረው ሳርም እዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ ለከብት ግጦሽም የሚሰጠው ጥቅም ዝቅተኛ ነበር። ቦታው ተራራማ እና ገላጣ ከመሆኑ የተነሳ ዓፈሩ በጎርፍ እየተሸረሸረ በመጎዳት ላይ ይገኝ ነበር። የተራራው ቦታ ከመሸርሸርም አልፎ በተራራው ስር ያሉ የእርሻ መሬቶች (ማሳዎች) ከተራራው የሚመጣ ጎርፍ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰባቸው ይገኝ ነበር። በመሆኑም በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎች በሰፈራ ስም በመነሳት በሌሎች ዞኖችና አካባቢዎች እንዲሰፈሩ በመደረጉ ከቦታው ለመፈናቀል ምክንያት ሆኖባቸው ነበር። ይህ በመከሰቱ ችግሩን ለመፍታት በመረባረብ የተለያዩ ጥረቶች ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል።

7.2.2. ቦታው ለተፋሰስ ስራ የተመረጠበት ምክንያት

የወልቂጤማ ኢብሳ ሳይት በህዝብ በተፋሰስ ስራ እንዲሰራበት የተመረጠበት ምክንያት ተራራማ ቦታ ሆኖ ገላጣ እና በጎርፍ ለመሸርሸር የተጋለጠ ቦታ በመሆኑ፣ አርሶ አደሮች ለትንሽ ጥቅም ሲሉ ቦታውን ለሰብል ምርት እያረሱት ችግሩ እየተባባሰ ቦታው ለከፍተኛ ጉዳት እየተጋለጠ ስለነበር፣ ዓፈሩ በጎርፍ የመሸርሸር ጉዳቱ እየጨመረ መምጣቱ፣ ቦታው ከራሱ ጉዳትም አልፎ በተራራው ስር ያሉ የእርሻ መሬቶች (ማሳዎች) ከተራራው በሚመጣ ጎርፍ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰባቸው ስለነበር እና በአጠቃላይ እየተፈጠረ ባለው ችግር ምክንያት በአካባቢው የነበሩ ነዋሪዎች እስከ መፈናቀል ስለደረሱ ቦታው ለተፋሰስ ስራው መመረጥ ችሏል።

7.2.3. በቦታው ላይ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች

የወልቂጤማ ኢብሳ ሳይትን የማልማት ስራ የተጀመረው በ2012 ዓ.ም ሲሆን ለ2 ዓመት ያህል ስራው ቢሰራም በዕቅድ የመምራቱ ሁኔታ እና ክትትሉ አናሳ ስለነበር ውጤታማነቱም ዝቅተኛ ነበር። በ2013 ዓ.ም መጨረሻው ዓመት ላይ የታሰበውና የተከናወነው ሲታይ ለውጡ ከችግር የማያወጣ መሆኑን በመገምገም በተጠናከረ ሁኔታ የተፋሰስ ስራውን ለመፈፀም ተወሰነ። በ2014 ዓ.ም በቦታው ላይ ምን መሰራት እንዳለበት ዕቅድ በማቀድ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የአፈሩን ባሕርይ መተከል ያለባቸው የችግኝ ዓይነቶች፣ መጠቀም የሚያስፈልጉትን ቴክኖሎጂዎች (የእርከን ዓይነት) የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ታሳቢ ያደረገ በባለሙያ የማስጠናት ስራ ተሰርቷል። የሚያስፈልጉ የመስሪያ ቁሳቁሶች እንደ ውሃ ልክ፣ ሜትር፣ ሲባጎ ገመድ፣ ችካል፣ ደንጎራ፣ ሞረድ የመሳሰሉት በየዓይነቱ ዝግጁ ተደርገ።

7.2.4. የተፈጠረ ግንዛቤ

ከዕቅድ በመቀጠል የተከናወነው ተግባር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ሲሆን የተሰጠው ግንዛቤም ውጤት አስመዝግቧል። እንደ ዶባ ወረዳ ለሁሉም ቀበሌዎች በዓመት 2 ጊዜ የግንዛቤ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን ለወልቂጡማ ሳይት ተፋሰስ ስራ ተሳታፊዎች በዓመት እስከ 624 (ወ 577 ሴ 47) ሰዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጓል። በተሰጠው ግንዛቤ ላይ የውይይት ርዕስ ሆነው የቀረቡትም በተራራው ላይ እየተፈጠረ ያለው ጉዳት አስከፊነቱ፣ ጉዳቱ በዚሁ ከቀጠለ የነዋሪው ቀጣይ ዕጣ-ፋንታ ምን እንደሚሆን፣ ምን መደረግ እንዳለበት የመፍትሔ ሀሳብ እና የስራ ድርሻን በመለየት የድርሻን ለመወጣት መግባባት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በዚህ ጥቅል ወይይት ላይ በተጨማሪ የቡድን ውይይት በማድረግ የተፋሰስ ስራው በትኩረት እንዲሰራ ተደርጓል።

7.2.5. የተከናወነ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ተግባር ስራ

የሚታዩ የአካባቢ መራቆት ችግሮችን በማጤን ለችግሮቹ መፍትሔ ለመስጠት በዕቅድ የተመሩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ወጥነት ባለው መልኩ ስራው እየተመራ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት የተቀናጀ የተፋሰስ ስራ ተሰርቷል።

ይህ የወልቂጡማ ኢብሳ ሳይት የተሰራው በሕብረተሰቡ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ነው። በተፋሰስ ልማቱ የተከለለው እና የለማው ቦታ ስፋቱ 380 ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 210 ሄክታሩ የወል መሬት ሆኖ በደን የተሸፈነ ነው። ቀሪው 170 ሄክታር ደግሞ የግለሰቦች ሆኖ የቦሮቦር ማገገም ስራ ተሰርቶበት እንደ ዝሆኔ ሳር እና ሌላ የእንስሳት መኖ ተተክሎበት በክልል ውስጥ ጥብቅ ሆኖ የቦታው ባለቤቶች በጥንቃቄ እየተጠቀሙበት ይገኛል።



ፎቶ3፡-የወለቂጡማ ኢብሳ ሳይት እርከን ስራ

በዚህ ቦታ ላይ በዋናነት ትኩረት ተደርጎበት የተሰራው የእርከን ስራ ሲሆን እርከኑ በድንጋይ እና በአፈር የተሰራ ነው። ስራው ሲሰራ ከተፈጥሮ ሀብት ስራ ጋር በማያያዝ ሕብረተሰቡን በፕሮግራም በማደራጀት እና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ነው።

የስራው ፕሮግራምም የነበረው በወር 12 ቀን ሆኖ በያንዳንዱ ቀን ለ5 ሠዓት ቆይታ ለመስራት በማቀድ እና በዕቅዱ መሰረት መከናወኑን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ነው። በስራው ላይ ወ 539 ሴ 154 ድ 693 ማህበረሰብ የተሳተፈ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ወ 417 ሴ 100 ድ 517 ተሳታፊዎች ቦታውን አልምተው በውጤቱም በባለቤትነት እንዲጠቀሙ የተደራጁ የማህበር አባላት ናቸው።

ሕብረተሰቡ በጉልበት ሲሰራ ባለሙያዎች ደግሞ ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ በጉልበትም ይሳተፋሉ። የግብርና ባለሙያ ስለ እርከኑ አሰራር ዲዛይን እና አይነት ሙያዊ ስራ ሲሰራ ጤና ኤክስቴንሽኖች ደግሞ የመጀመሪያ እርዳታ ማድረጊያ ነገሮችን(First Aid) ይዘው በስራው ላይ ሰራተኛ ከተጎዳ የመጀመሪያ ዕርዳታ ህክምና ያከናውናሉ። በዚህ ስራ ላይ ‹CALM P4R And PSNP› የሚባል ፕሮጀክትም የመቆፈሪያ መሳሪያ ገዝቶ በመስጠት እና ለኮሚቴዎች ስልጠና በመስጠት ድጋፍ አድርጓል። በዚሁ ስራ ላይ ቅንጅታዊ አሰራሩን በማጠናከር ፕሮግራም በማመቻቸት የግብርናን፣ የጤናን፣ የትም/ትን እና የጸጥታን ባለሙያዎች በመጠቀም የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን ከስራው ጋር ጎን ለጎን የማስተማር ስራ ተሰርቷል። ከስራ በኋላ የእለቱ ስራ ግምገማ ይደረግና በቀጣዩ ፕሮግራም ተነጋግሮ መግባባት ላይ ይደረሳል። በዚህ መሰረት ሕብረተሰቡ ቀድሞ በመግባባት አምኖበት እየሰራ ስለነበር ልማቱ በተነሳሽነት የተሰራ ነው።

ሕብረተሰቡን ከቴክኖሎጂ ጋር በማላመድ እንዲጠቀሙ ከማድረግ ጋር ተያይዞ በቀበሌው ለሚገኙ ሰዎች ስለ ሶላር እና ዘመናዊ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ጥቅም ግንዛቤ እንዲያገኙ ተደርጎ 465 አባወራዎች ሶላር ተጠቃሚ እና 231 አባወራዎች ዘመናዊ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ በግል ገዝተው ተጠቃሚ ሆነዋል።

የአካባቢው ነዋሪዎች በተገኘው መረጃ የተፋሰስ ስራው የተጀመረው በ2012 ዓ.ም መሆኑንና ቦታው ምንም የሌለው ገላጣ ለጎርፍ የተጋለጠ መሬት ነበር ማለት ነው። ቦታው ለልማት ከመከለሉ በፊት የእርሻ ቦታ ነበር። ተራራማ እና ገላጣ ከመሆኑ የተነሳ ጎርፉ እየተንደረደረ መሬቱ እየተሸረሸረ ነበር።

አሁን ቦታው በመልማቱ ምክንያት መሬቱ በጎርፍ ከመጎዳት ድኗል። ከተራራው ስር ያለ የእርሻ መሬትም ከተራራው የሚመጣ የጎርፍ ውሃ ቀንሶለታል። የአካባቢው የአየር ንብረትም ለኑሮ ምቹ ሆኗል። የተለያዩ የዕፅዋት ዝርያዎች እና ሳር በከፍተኛ ሁኔታ እየለማ በመሆኑ መሬቱን ከጎርፍ መሸርሸር ከማዳንም አልፎ ነዋሪው በውጤቱ እንዲጠቀሙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።

7.2.6. 3.6.ስራውን ለማጠናከር እና ለልማቱ ቀጣይነት የተደራጀ ማህበር

በቦታው ላይ የሚያለሙና በልማቱ በባለቤትነት መጠቀም የሚችሉ ወ 417 ሴ 100 ድ 517 የማህበር አባላት በ2012 ዓ.ም "ለሊስቱ መገሪሳ" በሚል የማህበር ስያሜ እንዲደራጁ ተደርጎ

ለማህበር አባላት ስራ በመፍጠር ቦታውንም በባለቤትነት እንዲያለሙ፣ እንዲንከባከቡ እና በውጤቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል። አባላቱም ንብ በማነብ፣ ሳር አጭዶ በመሸጥ ገቢ እንዲያገኙ ተደርጓል።

ማህበሩን ለማጠናከር በፕሮጀክት ድጋፍ 43 ዘመናዊ ቀፎ ተገዝቶ ተሰጥቷቸዋል። ከነዚህ ውስጥም 11 ቀፎዎች ንብ ያለባቸው ሲሆኑ ቀሪዎቹ ንቡ እየተባዛ ሲሄድ ሊጠቀሙበት ዝግጁ የሆኑ ናቸው። ማር የሚቆረጠው እንደ ወቅቱ ሁኔታ ሲሆን በ2017 ዓ.ም 40 ኪ.ግ ማር አግኝተዋል። ማህበሩ ከሳር ሽያጭ ገቢ እያገኘ ሲሆን በዓመት ከሳር ሽያጭ እስከ 83,000 ብር እንደሚያገኙ እና ገቢው ለማህበሩ ሆነዋልረ። የማህበር አባላቱ እርከን በመስራት፣ የችግኝ ጉድጓድ በማዘጋጀት፣ ችግኝ በመትከል፣ ቦታውን በመጠበቅ በሰውና በቤት እንስሳት ንክኪ እንዳይጎዳ ከአደጋ በማዳን፣ እያገገሙ ያሉትንና በአዲስ የተተከሉትን ችግኞች በመንከባከብ ለተፋሰስ ስራው እና ለቀጣይነቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረጉ ይገኛሉ።



ፎቶ4፡-የለሊስቱ መገሪሳ ማህበር ንብ እርባታ ቀፎ በከፊል

የ"ለሊስቱ መገሪሳ" ማህበር ሊቀመንበር የሆኑትን አቶ አብዱልጀሊል ማህበሩ የተደራጀው በ2012 ዓ.ም መሆኑን ገልፀው "መሬቱ በከፍተኛ በመጎዳቱ እና አካባቢው በረሃ ሆኖ ለኑሮ ምቹ ባለመሆኑ ምክንያት ህዝቡ ከቦታው ተፈናቅሎ ሙሉ በሙሉ ሊጠፋ ነበር። እርከን በመስራት፣ የችግኝ ጉድጓድ በማዘጋጀት፣ ችግኝ በመትከል፣ ቦታውን በመጠበቅ ከሰውና ከቤት እንስሳት ንክኪ ነጻ እንዲሆን በማድረግ፣ እያገገሙ ያሉትንና በአዲስ የተተከሉትን ችግኞች በመንከባከብ የተፋሰስ ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው እየሰራን ነው። ተባብረን በመስራታችን እና አብረን በማልማታችን የጋራ ተጠቃሚ ሆነናል ብለዋል።

በፊት የዝናብ እጥረት ያጋጥመን የነበረው አሁን ዝናብ በወቅቱ እየመጣልን ነው። ሦስት ምንጮች ጎልብተውልናል። በፊት የነበረው በረሃነት ተቀይሮ አሁን የአየር ንብረቱ ለጤና ምቹ ሆኗል። 43 ዘመናዊ ቀፎ ተገዝቶ ተሰጥቶናል። ከነዚህ ውስጥ 11ዱ ቀፎዎች ንብ አለባቸው። ማር የሚቆረጠው እንደ ወቅቱ ሁኔታ ነው። በ2017 ዓ.ም 40 ኪ.ግ ማር አግኝተናል።

ከሳር ሽያጭ በዓመት እስከ 83,000 ብር ገቢ እናገኛለን። ገቢውም ለማህበሩ ነው። አካባቢው እና የአየር ንብረቱ ለጤና ምቹ እንዲሆን በመንከባከብ በሚገኘውም ገቢ ተሻሽለን በተሻለ ሀብት ኑሮአችንን እየመራን ለወደፊት ወፍጮ እንዲሁም ትራክተር ገዝተን ከራሳችንም አልፈን የአካባቢውን ማህበረሰብ ለመጥቀም ዓላማ አድርገን እየሰራን እንገኛለን።" በማለት አቶ አብዱልጀሊል ገልፀዋል።

7.2.7. የተገኘ ውጤት

በተራራው ላይ የተሰራው እርከን ያበረከተው ዓፈሩ እንዳይሸረሸር እና መሬቱ እንዳይቦረቦር ብቻ ሳይሆን ውሃም በቦታው ላይ እንዲሰርግ በማድረግ እያገገሙ ያሉት እና በአዲስ የተተከሉት ዕጽዋቶችም ውሃ አግኝተው እንዲያለመልሙ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሰጥቷል።



ፎቶ5፡- በሳይቱ የተሰራው እርከን አሁን ያለበት ሁኔታ

በቦታው የተለያዩ ዕጽዋቶች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ድግጣ፣ የአበሻ ጥድ፣ ክትክታ፣ አኬሺያ፣ ዶዶሆ፣ ቁልቋል፣ እምቡስ፣ ግራቪሊያ፣ ማንጎ፣ ወይራ ወዘተ የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ናቸው።



ፎቶ6፡- በተከለለው ቦታ ላይ የሚገኙ እጽዋቶች በከፊል

ቦታው ተከልሎ እንክብካቤ በማግኘቱ እና በእጽዋት ተሸፍኖ ወደ ደንነት በመለወጥ ላይ በመገኘቱ የተለያዩ እንስሳቶች እና አእዋፎች በውስጡ መገኘት ችለዋል።



ፎቶ7፡-የተከለለው ቦታ ያለበትን ሁኔታ እና በውስጡ ያሉ እንሰሳዎችን ባለሙያዎች ሲገልፁ

በፊት ገላጣ ሆኖ በድርቀት የተጎዳ መሬት አሁን መሬቱ ላይ እርከን በመሰራቱ እና የእርከን አሰራሩ ቦታው ላይ ውሃ እንዲሰርግ የሚረዳ በመሆኑ እንዲሁም በአዲስ የተተከሉት ችግኞች እና ያገገሙት ነባር ዕጽዋቶች መሬቱን ሸፍነው ከድርቀት ከመጎዳት በማዳን በቦታው ላይ

የከርሰ-ምድር ውሃ እንዲፈጠር በማድረጉ በአካባቢው ሦስት (3) ምንጮች ጎልብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

7.2.8. ለውጤቱ ቀጣይነት የተዘረጋ ስርዓት

በአሰራሮች ላይ ጥብቅ ክትትል፣ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም የተሰሩ ስራዎችን በመገምገም በተሻለ ሁኔታ ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው ተደርጓል።አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ግለሰቦች በስራው ክትትልና ድጋፍ ላይ ተሰማርተው ለውጤቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

በክልል ውስጥ ገብቶ የቆረጠ፣ ከብት የለቀቀ ምን መቀጣት እንዳለበት መተዳደሪያ ደንብ አስቀምጠዋል። በዚህ መሰረት ከብት የለቀቀ ከ500 እስከ 1000 ብር እንደሚቀጣ በጋራ የተስማሙበት በመኖሩ ሁሉም ይጠነቀቃል።

የቦታው የባለቤትነት መብት ለማህበር አባላት መሰጠቱ የኔ ነው ብለው እንዲንከባከቡ ረድቷል።ስለዚህ ለቦታው ባለቤት ስለሆኑ ቦታውን በዋናነት የሚንከባከቡት እና የሚቆጣጠሩት በባለቤትነት የማህበሩ አባላት ናቸው።ቀሪው የአካባቢው ነዋሪም የስራው ውጤት፣የአየር ንብረቱን ያሻሻለለት፣ጎርፍን የቀነሰለት እንዲሁም ማሳው ምርቱ እንዲጨምር ምክንያት የሆነለት መሆኑን በመረዳቱ የልማቱ ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

የቀበሌ ቢሮ፣የአባገዳ ቢሮ እና የጤና ኤክስቴንሽን ጽ/ቤት በክልል ውስጥ በመኖሩ ለተለያየ ጉዳይ የሚመጡ ባለጉዳዮች ቦታውን በመጎብኘት፣የዛፎቹን ጥላ በመጠቀም እንዲሁም በፊት የነበረውንና አሁን የሚታየውን በማነጻጸር የስራቸውን ውጤት እያደነቁ ስላስገኘው ጠቀሜታ እየተነጋገሩ ነው። ይህም የልማቱ ውጤት ቀጣይነት እንደሚኖረው ያሳያል።



ፎቶ8፡- በወልቂጤማ ሳይት ክልል ውስጥ የሚገኙ ጽ/ቤቶች

7.3.ገመቺስ ወረዳ

ገመቺስ ወረዳ የሚገኘው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ሲሆን ወጣ ገባ እና ተራራማ የመሬት አቀማመጥ ያለው እና ወይነ ደጋ የአየር ንብረት ያለበት ወረዳ ነው። ወረዳው 35 ቀበሌዎች እና 3 ከተማ አስተዳደሮች አሉት። የወረዳው ሦስቱ ከተማ አስተዳደሮችም ቁኒ ከተማ፣ ድንገቴ ከተማ እና ደጋጋ ከተማ ሲሆኑ ዋናዋ የወረዳው ከተማ ቁኒ ትባላለች። የገመቺስ ወረዳ ሕብረተሰብ 85% በግብርና ስራ፣10% ከፊል አርብቶ አደር እና 5% በንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ኑሮአቸውን የሚመሩ ናቸው። የወረዳው ህዝብ ብዛት ወ 143,023 ሴ 137,414 ድ 280,437 ናቸው። የገመቺስ ወረዳ በአሁኑ ወቅት የውሃ ሀብት ያለው ሆኖ ከወረዳው የወጣው ውሃ ለገመቺስ ብቻ ሳይሆን ለደበሶ፣ ለሜኤሶ፣ ለአልበረከቴ እና ለሜሮ ከተማ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

በ1995 ዓ.ም እና በፊት አካባቢው ድርቅ እና መሬቱ በጎርፍ የታጠበ ስለነበር በርካታ አባወራዎች ተፈናቅለው ወደ ወለጋ እና ኢሉባቡር ሔደዋል። ችግሩን ለመግታት ሲባል በወቅቱ ህዝቡን ለማደራጀት ቢሞከርም አንደራጅም ብለው የሄዱ አሉ። የቀሩት ግን በወረዳው አመቻችነት ተደራጅተው አከባቢያቸውን አልምተው ተጠቃሚ ሊሆኑ ችለዋል።

በዞኑ ስር ካሉት ወረዳዎች ውስጥ የተሰሩ የተፈጥሮ ሀብት ስራዎችን በ2016 ዓ.ም እና በ2017 ዓ.ም ክልሉ በማየት ገመቺስ ወረዳ በተሻለ ውጤታማነት ተመርጦ በክልል ፕረዘዳንት ጽ/ቤት የመኪና ተሸላሚ ሆኗል።

7.3.1. በተፋሰስ ስራ ላይ በወረዳው የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ምዕራብ ሐረርጌ ዞን ተራራዎችን ማልማትና ከጉዳት ማዳን አለብኝ ብሎ በመነሳት በየደረጃው ዕቅዶችንና ግንዛቤዎችን ሲያወርድ ትኩረት ከሰጠባቸው ቦታዎች ውስጥ አንዱ ገመቺስ ወረዳ ነው።

ገመቺስ ወረዳም ከሚፈጠሩ ጉዳቶች ለመዳን ለተፋሰስ ስራው ትኩረት ሰጥቶ ከወረዳ እስከ መንደር ህዝቡን አዋቅሮ የስራ ቡድን በመመስረት መከናወን ያለበትን በየደረጃው አቅዶ ለአመራሩ፣ ለባለሙያዎች፣ ለሀገር ሽማግሌዎች፣ ለማህበር አባላት እና ለማሕበረሰቡ በዕቅዱ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ መተማመን ላይ ደርሶ ወደ ስራ መግባት ችሏል። ማሕበራትን በማደራጀትና የማህበሩን አባላት በመለየት ወደ ስራ የማስገባት የመምራት፣ የመደገፍ እና የማስተባበር ስራ በመስራት በስራው ላይ ሁሉም ትኩረት እንዲሰጡ ተደርጓል። የተፋሰሱን ስራ ለማከናወን የጊዜ ሰሌዳ በማቀድ ክንውኑን በመከታተልና በመገምገም ስራዎች በትኩረት እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጧል። በዚህ መሰረት የሚታዩ ችግሮችን በማጤን እና ለችግሮቹ መፍትሔ በመስጠት በዕቅድ የተመሩ ተግባራት ተከናውነዋል። ከዕቅድ በመቀጠል የተከናወነው የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ሲሆን የተሰጠው ግንዛቤም ውጤት አስመዝግቧል። እንደ ገመቺስ ወረዳ በዓመት ከ500 እስከ 800 ሰዎች በግንዛቤው ተሳትፈዋል።

1. **በገመቺስ ወረዳ 5 ችግኝ ጣቢያዎች ያሉ ሲሆን በያንዳንዱ ችግኝ ጣቢያ የራሳቸው ሰራተኞች አላቸው። እነሱም፤**

2. ዘገራያ ችግኝ ጣቢያ ያሉት የሰራተኛ አባላት ወ 16 ሴ 9 ድ 25
3. ከደና ችግኝ ጣቢያ ያሉት የሰራተኛ አባላት ወ 5 ሴ 4 ድ 9
4. ቀበነአ ችግኝ ጣቢያ ያሉት የሰራተኛ አባላት ወ 14 ሴ 12 ድ 26
5. ስሬ ቀለሞ ገቶ ችግኝ ጣቢያ ያሉት የሰራተኛ አባላት ወ 8 ሴ 3 ድ 11
6. ካሴ ችግኝ ጣቢያ ያሉት የሰራተኛ አባላት ወ 8 ሴ 2 ድ 10 ናቸው።

እነዚህ አምስቱ ችግኝ ጣቢያዎች ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሌሎች በቅርንጫፍነት የሚሰሩ በወረዳው ይገኛሉ።ለችግኝ ጣቢያዎቹ ሰራተኞች በየወሩ የሚከፈላቸው ሲሆን ለያንዳንዱ 3,600 ብር በወር ይከፈላቸዋል። በዚህም መሰረት ሴቶችና ወጣቶች የስራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። የሕብረተሰቡ አስተሳሰብ ተሻሽሎ በተነሳሽነት የድርሻቸውን በመወጣታቸው ዛሬ ከድሮው ተሻሽሎ በአረንጓዴ የተሸፈኑ ተራራዎች በወረዳው ማየት ተችሏል። በገመቺስ ወረዳ ካሉት ቀበሌዎች ውስጥ የድንገቴ ቀበሌን በመስክ ምልከታው ማየት ተችሏል።

7.4. ድንገቴ ባድያ ቀበሌ

የድንገቴ ቀበሌ ጽ/ቤት ከወረዳው ቁኒ ከተማ 20 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። ቀበሌው ወጣ ገባ እና ተራራማ የመሬት አቀማመጥ ያለው እና ወይነ ደጋ የአየር ንብረት ያለበት ቀበሌ ነው። የቀበሌው ህዝብ አብዛኛው በግብርና ስራ እና ጥቂቶቹ በከፊል አርብቶ አደር ተሰማርተው ኑሮአቸውን የሚመሩ ይገኛሉ። በድንገቴ ቀበሌ የሚኖሩ ነዋሪዎች አካባቢያቸውን ከጉዳት ለማዳን ሲሉ የሰሩት በርካታ የተፋሰስ ስራ ያለ ሲሆን ከተሰሩት ውስጥ የድንገቴ ባድያ ሳይትን ማየት ተችሏል።

7.4.1. የተፋሰስ ስራው ከመጀመሩ በፊት የድንገቴ ባድያ ሳይት የነበረበት ሁኔታ

የድንገቴ ባድያ ሳይት በተፋሰስ ስራው ከመልማቱ በፊት ገላጣ የሆነ ለጎርፍ የተጋለጠ ቦታ ነበር። በመሬቱ ላይ እየበቀለ የነበረው ሳርም ለከብት ግጦሽ የሚሰጠው ጥቅም ዝቅተኛ ነበር። ቦታው ተራራማ እና ገላጣ ከመሆኑ የተነሳ ዓፈሩ በጎርፍ እየተሸረሸረ በመጎዳት ላይ ይገኝ ነበር። የተራራው ቦታ ከመሸርሸርም አልፎ በተራራው ስር ያሉ የእርሻ መሬቶች (ማሳዎች) ከተራራው የሚመጣ ጎርፍ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰባቸው ይገኝ ነበር። በዚህም ምክንያት በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች ከቦታው ለመፈናቀል አንድ ምክንያት ነበር። በመሆኑም ይህንን ችግር ለመፍታት በመረባረብ የተለያዩ ጥረቶች ማድረግ ግድ ሆኗል።

7.4.2. ቦታው ለተፋሰስ ስራው የተመረጠበት ምክንያት

የድንገቴ ባድያ ሳይት በህዝብ የተፋሰስ ስራ እንዲሰራበት የተመረጠበት ምክንያት ተራራማ ቦታ ሆኖ ገላጣ እና በጎርፍ ለመሸርሸር የተጋለጠ ቦታ በመሆኑ፣ ዓፈሩ በጎርፍ የመሸርሸር ጉዳቱ እየጨመረ መምጣቱ፣ ቦታው ከራሱ ጉዳትም አልፎ በተራራው ስር ያሉ የእርሻ መሬቶች (ማሳዎች) ከተራራው በሚመጣ ጎርፍ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰባቸው ስለነበር እና በአጠቃላይ እየተፈጠረ ባለው ችግር ምክንያት በአካባቢው የነበሩ ነዋሪዎች እስከ መፈናቀል ስለደረሱ ቦታው ለተፋሰስ ስራው መመረጥ ችሏል።

7.4.3. በቦታው ላይ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች

በሳይቱ ላይ ስለሚሰሩ ስራዎች ቀድሞ ግንዛቤ በማስጨበጥ በርካታ የተግባር ስራዎች ተሰርተዋል። በድንገቴ ባድያ ሳይት ላይ በፊት እየተፈጠረ ያለውን የመሬት መጎዳት በዝምታ ማየት ችግሩን እያባባሰው መጥቷል። በመሆኑም ችግሩን የጋራ አድርጎ በጋራ መፍታት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። በዚህ መሰረት በማህበረሰቡ ውይይት ተደርጎበት የስምምነት ፊርማ ተከናውኖ በአመራሩ ማስተባበር፣ በባለሙያው ድጋፍና በሕብረተሰቡ ተሳታፊነት የድንገቴ ባድያ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራ በ2012 ዓ.ም ተጀምሯል። ስራውም በታቀደው መሰረት ስለመከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት የተፋሰስ ልማቱ ተሰርቷል።

የድንገቴ ባድያ ሳይት የተፋሰስ ስራ የተሰራው በሕብረተሰቡ መረባረብ ነው። የተከለለው እና የለማው ቦታ ስፋቱ 232 ሄክታር ሲሆን የሁሉም ቦታ ባለቤት የተደራጁት የማህበር አባላት ናቸው። በዚህ ክልል ቦታ ላይ የአፈር እርከን ተሰርቷል። የተሰራው እርከን ሲሸረሸርና ሲንሸራተት የነበረውን ዓፈር በመክተር አሁን ጎድጓዳው ቦታ ሞልቶ የአፈሩ መንሸራተት ቀርቶ ሳር እና ሌላ እጽዋት በቅሎበት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።



ፎቶ9፡-በዓፈር እርከን የተሰራበት ቦታ አሁን ያለበት ሁኔታ

ስራው ሲሰራ ከተፈጥሮ ሀብት ስራ ጋር በማያያዝ ሕብረተሰቡን በፕሮግራም በማደራጀት እና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ነው። በወረዳና በቀበሌ ቴክኒካል ኮሚቴ ተቋቁሞ ስልጠናም ተሰጥቶ ድጋፍ እየተደረገ ስራው በአግባቡ እንዲመራ ተደርጓል። በስራው ላይ ሁሉም የቀበሌው ነዋሪዎች የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ወ 96 ሴ 15 ድ 111 ተሳታፊዎች ቦታውን አልምተው በውጤቱም በባለቤትነት እንዲጠቀሙ የተደራጁ የማህበር አባላት ናቸው። አመራሮች እያስተባበሩ ሕብረተሰቡ በጉልበት ሲሰራ ባለሙያዎች ደግሞ ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ በጉልበትም ይሳተፋሉ። በዚሁ ስራ ላይ ቅንጅታዊ አሰራሩን በማጠናከር ፕሮግራም በማመቻቸት

ከስራ በኋላ የእለቱ ስራ ግምገማ ይደረግና በቀጣዩ ፕሮግራም ላይ ተነጋግሮ መግባባት ላይ ይደረሳል። በዚህ መሰረት ሕብረተሰቡ ቀድመው በመግባባት አምኖበት እየሰራ ስለነበር ልማቱ በተነሳሽነት የተሰራ ነው።

በቀበሌአ እና ዘገሪያ ችግኝ ጣቢያዎች ችግኝ አቅራቢነት በቦታው ላይ የጥድ ችግኝ በ2015 ዓ.ም በህብረተሰቡ ተተክሏል። ከነዚህ ሁለቱ ችግኝ ጣቢያዎች የተወሰደበት ምክንያትም ለቦታው በቅርበት የሚገኙ በመሆናቸው ነው። ችግኝ የተተከለበት መሬት ዓፈሩ ተመርምሮ እና ቦታው በጂፒኤስ (GPS) ተጠንቶ የተዘጋጀ ነው።



ፎቶ10፡-የተተከሉ ችግኞች አሁን ያሉበት ሁኔታ

በቦታው ላይ ያሉት በአዲስ የተተከሉ ዕጽዋቶች ብቻ ሳይሆኑ አገግመው እንደገና ያደጉ እጽዋቶችም በሰፊው የሚገኙ ሲሆን ጥድ፣ አዛምር፣ ብሳና፣ ዝግባ፣ ቀለህ፣ ከሴ፣ አጋም፣ ግራዋ፣ ቀጋ፣ ድግጣ እና ያደገ ሳር ይገኛል።



ፎቶ11፡-በተከለለው ቦታ ላይ ያገገሙ እና አዲስ የተተከሉ እጽዋቶች ያሉበት ሁኔታ

በቦታው ላይ ካሉት የሳር ዝርያዎች ውስጥ ሰንበሌጥ በጣም አምሮበት የሚታየው የሳር ዝርያ ነው።



ፎቶ12፡- ቦታው አሁን አገግሞ ያበቀለው የሰንበሌጥ ሳር በከፊል

ቦታው በተጎዳበት ወቅት ችግሩን ተቋቁመው ከመውደም የተረፉ የዝግባ ዛፎች አሁንም በናሙናነት ይታያሉ።



ፎቶ13፡-ከመውደም የተረፉ ነባር የዝግባ ዛፎች

በተከለለው ቦታ ውስጥ የተለያዩ እንስሳቶች እና አዕዋፎች የሚገኙ ሲሆን ድኩላ፣ ሚዳቆ፣ ከርከሮ፣ አሳማ፣ ነብር/አነር፣ ጅብ እና የተለያዩ አዕዋፎች ለምሳሌ የሚጠቀሱ እንደሆኑ ናቸው። ቦታው እንደተከበረ በቀጣይነት ለማቆየት በሰውና በቤት እንስሳት እንዳይጎዳ እየተጠበቀ ይገኛል።

የአካባቢው ነዋሪ የሆኑትን አርሶ አደር የሆኑት አቶ ሻንበል ከበደ ተጠይቀው እዚህ ቦታ ላይ ችግኝ በተተከለበት ወቅት የቀበሌው አስተዳደር እንደነበሩ ገልጸውልን በቦታው ላይ የተቀናጀ የተፋሰስ ስራው ከመሰራቱ በፊት ገላጣ ቦታ ሆኖ በጎርፍም እየታጠበ የተጎዳ መሬት እንደነበር ገልጸዋል። ይህንን በማየት ከዞን እና ከወረዳም ድጋፍ የተቀናጀ የተፋሰስ ስራው በ2012 ዓ.ም ተጀምሮ እንደተሰራ እና በመቀጠልም በ2015 ዓ.ም አብዛኛው ችግኝ እንደተተከለ ገልጸዋል። ቦታው አሁን ከቤት አንስሳት እና ከሰው ንክኪ ጥብቅ ሆኖ የሚገኝ መሆኑን እና የተለያዩ እንስሳቶችም በውስጡ እንደሚገኙ ገልጸው ቦታው በመልማቱ ዝናብ በአግባቡ በበቂ ሁኔታ እንዲያገኙ፣ የአየር ንብረቱ ጥሩ እንዲሆንላቸው እንዲሁም በአካባቢው 10 ምንጮች እነዲፈጠርላቸው የተቀናጀ የተፋሰስ ስራው ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ አንስተዋል።

7.4.4. ስራውን ለማጠናከር እና ለልማቱ ቀጣይነት የተደራጀ ማህበር

በድንገቴ ቀበሌ በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የሚሰራ አንድ ማህበር ያለ ሲሆን "ሚሶማ ቦሶና ኢፋ ባሲ" በሚል የማህበር ስያሜ እንዲቋቋም ተደርጎ ለተደራጁት የማህበር አባላት ስራ በመፍጠር የተቀናጀ የተፋሰስ ስራ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል። ማህበሩ ወ 96 ሴ 15 ድ 111 አባላት አለው። አሁንም የማህበሩ አባል ለመሆን የሚፈልግ ነዋሪ ወደ ማህበሩ ከመጣ አይከለከልም። ማህበሩም ከክልል ቦታው ላይ ከሚገኘው የሳር ሽያጭ ገቢ ለአባላት ብድር በመስጠት አባላቱ ፍየል በማርባት እና በሬ በማድለብ የትርፍ ስራ እየሰሩ ብድራቸውን ለማህበሩ ይመልሳሉ።ይህ ማህበር እስከ አሁን(ጥቅምት 2018 ዓ.ም) ለ100 አባላት ብድር ሰጥቶ 60ዎቹ ሲመልሱ 40ዎቹ ገና ያልመለሱ ናቸው። ማህበሩ በ2017 ዓ.ም 30 ፍየሎች ለ15 አባላትም ገዝቶ ሰጥቷል። የአካባቢው ነዋሪዎች ደን ይጨፈጭፉ የነበረው ገቢ ፍለጋ ስለነበር በአደረጃጀቱ የስራ ዕድል መፈጠሩ ችግሩን ቀንሶታል። ማህበሩ በዓመት እስከ 100,000 ብር ከሳር ሽያጭ ገቢ እንደሚያገኝ እና ከሚያገኘው ገቢም ለት/ቤት፣ ለቀበሌ ጽ/ቤት፣ ለአቅመ ደካማ ሰዎች፣ ለተቸገሩ ተማሪዎች ደብተር እና ቦርሳ በመግዛት ድጋፍ እያደረገ የረገኛል።

7.4.5. የተገኘ ውጤት

በተራራው ላይ የተሰራው እርከን ያበረከተው ዓፈሩ እንዳይሸረሸር እና ውሃም በቦታው ላይ እንዲሰርግ በማድረግ እያገገሙ ያሉት ነባሮቹ እና በአዲስ የተተከሉት ዕጽዋቶች ውሃ አግኝተው እንዲያለመልሙ ከፍተኛ ጠቀሜታ ሰጥቷል። ቦታው ተከልሎ እንክብካቤ በማግኘቱ እና በእጽዋት ተሸፍኖ በመገኘቱ የተለያዩ እንስሳቶች እና አእዋፎች በውስጡ መገኘት ችለዋል።

በፊት ገላጣ ሆኖ በድርቀት የተጎዳ መሬት አሁን መሬቱ ላይ እርከን በመሰራቱ እና የእርከን አሰራሩ ቦታው ላይ ውሃ እንዲሰርግ የሚረዳ በመሆኑ እንዲሁም በአዲስ የተተከለው ችግኝ እና ያገገመው ነባር ዕጽዋት መሬቱን ሸፍኖ ከድርቀት ከመጎዳት በማዳን ቦታው የከርሰ-ምድር ውሃ

እንዲፈጥር በማድረጉ በአካባቢው አስር (10) ምንጮች ጎልብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።



ፎቶ14፡-በልማቱ መሰራት ምክንያት የተፈጠሩ ምንጮች በከፊል

7.4.6. ቦታው አሁን ያለበት ሁኔታ

በሁሉም ተነሳሽነት፣ በአመራሩ ማስተባበርና መምራት፣ በባለሙያው ሙያዊ ድጋፍ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ተሳታፊነት በተቀናጀ የተፋሰስ ስራው ላይ ሁሉም የድርሻቸውን ተግባራት በማከናወናቸው የድንገቴ ባድያ ሳይት ዛሬ ከድሮው ተሻሽሎ በአረንጓዴ የተሸፈነ፣ የተለያዩ እፅዋቶች እና እንስሳቶች የሚገኝበት፣ ደርቀው የነበሩ ምንጮች ተመልሰው ያነለበቱበት እና ከስሩ ለሚገኙ የእርሻ መሬቶች በጎርፍ እንዳይጎዱ በማድረግ ምርታቸው እንዲጨምር በማድረግ የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከፍ ያደረገ ቦታ ሆኗል።



ፎቶ15፡-በልማቱ መሰራት ምክንያት ቦታው አሁን ያለበት ሁኔታ በከፊል

7.4.7. ለውጤቱ ቀጣይነት የተዘረጋ ስርዓት

በአሰራሮች ላይ ጥብቅ ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም የተሰሩ ስራዎችን በመገምገም በተሻለ ሁኔታ ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው ተደርጓል። አመራሮችና ባለሙያዎች እንዲሁም የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ግለሰቦች በስራው ክትትልና ድጋፍ ላይ ተሰማርተው ለውጤቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።ግንዛቤ ሲፈጠር ‹አትንካ ሳይሆን ያንተው ነው እየተንከባከብክ ተጠቀም› በሚል ለማህበር አባላት መሰጠቱ በባለቤትነት እንዲንከባከቡ ረድቷል። ለቦታው ባለቤት ስለሆኑ ቦታውን በዋናነት የሚንከባከቡት እና የሚቆጣጠሩት የማህበሩ አባላት ናቸው። ቀሪው ሕብረተሰብም የስራው ውጤት የአየር ንብረቱን ያሻሻለለት፣ ጎርፍን የቀነሰለት እንዲሁም ማሳው ምርቱ እንዲጨምር ምክንያት የሆነለት መሆኑን በመረዳቱ የልማቱ ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

በጥብቅ ክልል ውስጥ ከብት ገብቶ ቢገኝ ማህበረሰቡ በወሰነው መሰረት ባለቤቱ ይቀጣል። አንድ ከብት በክልሉ ገብቶ ቢገኝ ባለቤቱ የማህበሩ አባል ከሆነ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በአንድ ከብት 200 ብር የሚቀጣ ሲሆን ባለቤቱ የማህበሩ አባል ካልሆነ ደግሞ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በአንድ ከብት 400 ብር ይቀጣል። ቅጣቱ የተለያየበት ምክንያት ሰዎችን ለአባልነት ከማበረታታት አንጻር ነው።

7.5. በዶባ እና በገመቺስ ወረዳዎች ከታዩት የተፋሰስ ስራ ውጤቶች ውስጥ ሊወሰድ የሚገባ ተሞክሮ

- ለተፋሰስ ስራው ትኩረት ሰጥቶ ከወረዳ እስከ መንደር ድረስ የስራ ቡድን በመመስረት መከናወን ያለበትን በየደረጃው አቅዶ ለአመራሩ፣ ለባለሙያዎች፣ ለሀገር ሽማግሌዎች፣ ለተደራጁ ማህበር አባላት እና ለማሕበረሰቡ በዕቅዱ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር መተማመን ላይ መደረሱ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ አስችሏል።
- በመደገፍ እና በማስተባበር እንዲሁም ክንውኑን በመከታተልና በመገምገም ስራው ስለተመራ የተፋሰስ ስራው በትኩረት እንዲሰራ አድርጎታል ።
- ዕቅድ ክንውንን በመገምገም ለውጡ ከችግር የማያወጣ መሆኑን አውቆ በትኩስ መንፈስ የተፋሰስ ስራውን ለማሰራትና ለመስራት ስምምት ላይ መደረሱ አሁን ለተገኘው ውጤት አብቅቷል።
- የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ታሳቢ በማድረግ በቦታው ላይ ምን መሰራት እንዳለበት በማቀድ የመሬቱን አቀማመጥ፣ የዐፈሩን ባሕርይ፣ መተከል ያለባቸው የችግኝ ዓይነት፣ መጠቀም የሚያስፈልጉትን ቴክኖሎጂዎች (የእርከን ዓይነት)፣ በባለሙያ የማስጠናት ስራ መሰራቱ የተተከሉት ችግኞች በሙሉ እንዲፀድቁ ከመርዳትም አልፎ የታሰበው ዓላማ ስኬታማ እንዲሆን ረድቷል።
- ወደ ተግባር ከመገባቱ በፊት እና በስራ ሂደቱ ወቅት የግንዛቤ ፈጠራ ስራ መከናወኑ የስራው ተሳታፊዎች በተነሳሽነት እንዲሰሩ ረድቷል።
- "ተባብረን በመስራታችን እና አብረን በማልማታችን የጋራ ተጠቃሚ ሆነናል" የሚሉ የማህበር አባላት መፈጠራቸው የተፈጠረን ግንዛቤ ውጤቱን በተግባር ማሳየት ተችሏል።

- ሕብረተሰቡ በጉልበት ሲሰራ ባለሙያዎች ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ በጉልበትም መሳተፋቸው፣ ጤና ኤክስቴንሽኖች በቦታው በመገኘት የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጠታቸው የህብረተሰቡን ቅንጅታዊ አሰራር አጠናክሮታል።
- ከስራ በኋላ የእለቱ ስራ መገምገሙ እና ለቀጣዩ ፕሮግራም ተነጋግሮ መግባባት ላይ መደረሱ ስራው በተነሳሽነት እንዲሰራ አግዟል።
- በቀበሌው ለሚገኙ ሰዎች ስለ ሶላር እና ዘመናዊ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ጥቅም ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉ እና አቅርቦት መፈጠሩ ተጠቃሚዎች ተገንዝበው ዕቃውን በግል ገዝተው መጠቀም መቻላቸው የደን ጭፍጨፋን፣ የአየርብክለትን እና የእናቶች ጉዳትን ለመቀነስ ረድቷል።
- በተለያየ ቦታ ችግኝ ጣቢያዎች በማመቻቸት የችግኝ አቅርቦት በቅርበት እንዲገኝ መደረጉ የማጓጓዣ ወጪን መቀነስ እና የዓፈሩን ባህርይ የተላመደ ችግኝ ማግኘት መቻሉ ተጠቃሚዎችን ረድቷል።
- ከመፈናቀል የተረፈን ማህበረሰብ ራሳቸውን በማደራጀት እና ድጋፍ በማድረግ ችግሩ በራሳቸው እንዲፈታ አድርጎ ዛሬ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ የአመራሩን ጥንካሬ ያሳያል።
- ቀበሌው ያደራጃቸው እና ድጋፍ አድርጎላቸው ያጠናከራቸው ማህበራት አቅም አግኝተው ተመልሰው የቀበሌውን ማህበራዊ ተቋም መርዳት መቻላቸው ብዙዎቹን ያስተምራል።
- በፊት የተጎዳ መሬት እንክብካቤ ሲያገኝ የተሻለ ሳር አብቅሎ ከሳሩ ሽያጭ የተሻለ ገቢ መገኘቱ መሬትን መንከባከብ ከጎርፍ ለማዳን ብቻ ሳይሆን ከሚያስገኘው ውጤትም የተሻለ ገቢ ማግኘት እንደሚቻል ማህበረሰቡን አስተምሮታል።
- ውሃ ለመቋጠር የተቸገረ ተራራማ ቦታ ላይ ውሃ እንዲያሰርግ የሚረዳ እርከን መስራት ቦታው በላዩ ላይ ለሚተከል ዕጽዋት ምቹ ሆኖ ከመልማቱም አልፎ ምንጮችም እንዲጎለብቱ አስተዋፅኦ እንዳለው መረዳት ይቻላል።
- በቦታው መልማትና በዕጽዋቱ ማገገም የተነሳ የተለያዩ እንስሳቶች እና አእዋፎች በአካባቢው እንዲገኙ እንደሚረዳ ማየት ተችሏል።
- ተራራማ ቦታ ከተራቆተ ለእርሻ መሬት ጎጂ ከለማ ግን ጠቃሚ መሆኑን ከተራራው ስር ይሉ የእርሻ መሬቶች ምስክር ሰጥተዋል።
- ግንዛቤ ሲፈጠር አትንካ ሳይሆን የናንተው ነው እየተንከባከባችሁ በውጤቱ ተጠቀሙ በሚል የተከለለው ቦታ ለማህበር አባላት መሰጠቱ የባለቤትነት ስሜትን ስለፈጠረ በራስ ተነሳሽነት እንዲያለሙ እና እንዲንከባከቡ እንዲሁም ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ አድርጎታል።
- በወልቂጤማ ኢብሳ ቀበሌ የአባገዳ ቢሮ፣ የቀበሌ ቢሮ እና የጤና ኤክስቴንሽን ጽ/ቤት በተከለለው ቦታ ውስጥ እንዲሆን አድርጎ ለተለያየ ጉዳይ የሚመጡ ባለጉዳዮች ቦታውን በመጎብኘት፣ የዛፎቹን ጥላ በመጠቀም እንዲሁም በፊት የነበረውንና አሁን የሚታየውን በማነጻጸር የስራቸውን ውጤት እያደነቁ ስላበረከተው ጠቀሜታ እንዲነጋገሩ እድል መፈጠሩ የልማቱ ውጤት ቀጣይነት እንዲኖረው ያደርጋል።

- **በገመቺስ ወረዳ ዙሪያ ያሉት ስፍራዎች በተሰራው የተፋሰስ ስራ ምክንያት የውሃ ተጠቃሚ መሆናቸው የሚያስገነዝበው የተጎዱ ቦታዎችን በመንከባከብ እንዲያገግሙ ማድረግ ጥቅሙ ላገገመው ውስን ክልል/ቦታ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ለሚገኙ ስፍራዎችም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።**
- **በዞኑ ስር ባሉት ወረዳዎች የተሰሩ የተፋሰስ ስራዎችን በመጎብኘት በአንፃራዊ ከታዩት የተሻለ ውጤታማ ለተባለው ወረዳ የመኪና ተሸላሚ ማድረግ የተሸለሙትን ከማበረታታት አልፎ ሌሎችን እንዲነቃቁ ያደርጋል።**

ክፍል ሦስት

8. ማጠቃለያ

አፈር፣ ውሃ፣ እና አየር የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ናቸው። ዕፅዋት እና እንስሳት እኛን ጨምሮ በህይወት ለመኖር የነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች አስፈላጊነት ግድ ነው። ስለዚህ አካባቢ እንዳይጎዳ በማሰብ ብቻ ሳይሆን ለኛም በህይወት ለመኖር በማሰብ እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶቻችን እንዳይጎዱ የመንከባከብ ግዴታ አለብን። ለዓፈር እንክብካቤ ባለማድረግ፣በዕፅዋት መመናመን፣ በልቅ ግጦሽ እና በመሳሰሉት ምክንያት አካባቢ ይጎዳል። የውሃ እጥረትም ይከሰታል። በዚህ የተነሳ የአካባቢው ስነ-ምህዳር ለጉዳት ተጋልጦ የአየር ንብረቱ በመዛባት የዕፅዋትና እንስሳት ጤንነት ችግር ይከሰታል።

የዶባ ወረዳ ወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ እና የገመቺስ ወረዳ ድንገቴ ባድያ ቀበሌ ይህንን በማሰብ የሕብረተሰቡን አስተሳሰብ አሻሽለው የተቀናጀ የተፋሰስ ስራዎችን በመስራት በአረንጓዴ የተሸፈነ፣ የተለያዩ እፅዋቶች እና እንስሳቶች የሚገኙበት፣ ደርቀው የነበሩ ምንጮች ተመልሰው ያጎለበቱበት እና ከስሩ ለሚገኙ የእርሻ መሬቶች ጎጂ መሆኑ ቀርቶ ጠቃሚ በመሆን የሕብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከፍ ያደረገ ቦታ ፈጥረዋል።

በሁለቱም ቀበሌዎች የተቀናጀ የተፋሰስ ስራ ተሰርቶ ውጤት ሊመዘግብ የቻለው በአንድ አካል በተናጠል ተሰርቶ አይደለም። ዕቅድ ክንውን የተሳካው እና ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው የሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው የድርሻቸውን ስለተወጡ ነው። ከቀበሌው ሕብረተሰብ እና አመራሮች ተሳትፎ ተጨማሪ ከክልሉ፣ ከዞኑ እና ከወረዳው በልማቱ ክንውን ላይ የተለያየ ድጋፍ ተደርጓል።

አንድን ስራ ሰርቶ ውጤት ለማስመዝገብ በሁሉም ደረጃ ያሉ ሰራተኞች ትስስራቸውን አጠናክረው የድርሻቸውን ሚና መጫወት ዋንኛው እንደሆነ ከወልቂጡማ ኢብሳ ቀበሌ እና ከድንገቴ ባድያ ቀበሌ መማር ይቻላል። በታየው ቦታ ላይ ለውጡ የመጣውና የልማቱ ውጤት የተመዘገበው ግንዛቤ ተፈጥሮ ግንዛቤውን ወደተግባር ለመለወጥ በመግባባትና በቅንጅታዊ ስራ ስለተሰራ ነው። ሕብረተሰቡ ቀድሞ ግንዛቤ ባይፈጠርለትና መግባባት ላይ ባይደርስ ኖሮ በግዳጅ ልማቱ ላይ ቢሳተፍም ለውጡ ዘላቂነት አይኖረውም ነበር። በመሆኑም የጉዳዩን ትኩረት በግንዛቤ

የጋራ አድርጎ ወደተግባሩ መግባትና ልማቱን ማልማት ለውጡ ዘላቂነት እንዲኖረው አድርጎታል።

ስለዚህ ሁላችንም ያለንበትን ቦታ ነባራዊ ሁኔታ በማየትና በማጥናት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እየታገዝን ተፈጥሮ የሰጠችንን ሀብት በአግባቡ በመያዝና በመንከባከብ ተጠቃሚ መሆን አለብን። ወልቂጤማ ኢብሳ ቀበሌ እና ድንገቴ ባድያ ቀበሌ ልማቱን ያከናወኑት ሁሉ ነገር ተመቻችቶላቸው ሳይሆን የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን በጋራ ታግለው በመፍታት ነው። በመሆኑም እኛም "ይቻላል" የሚል ስንቅ ሰንቀን አካባቢያችንን በመንከባከብ እና በማልማት ለጤና ምቹ እንዲሆን በማድረግ ሊከሰት ከሚችለው የአየር ንብረት ለውጥ አደጋ መዳን ይጠበቅብናል።